ቀን፡- 14 ጥር 2006 ዓ.ም

# *የአያቶች መንገዶችን መዝጋት ዘመቻ - ወደ ከተማ ደሴትነት የሚደረግ ጉዞ*

(በኃይለመለኮት አስፋው)

(E-mail:- hailemelekot2003@yahoo.com)

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነው ጉዳይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአያት ሪል እስቴት ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እየተደረገ ያለውን በርካታ የመተላለፊያ መንገዶችን በወርዳቸው እና ቁመታቸው ትልልቅ በሆኑ የብረት አጥሮች የመዝጋት ዘመቻ እውነተኛ ምክንያት እና በአካባቢው ባሉ ነዋሪዎች በተለይ በሪል እስቴቱ አዋሳኝ በሆኑ ሰፈሮች በሚኖሩ ዜጎች ከዚያም አልፎ ከሌሎች የከተማዋ አካባቢ ለስራ ጉዳይ ሆነ ዘመድ ጥየቃ በሚመጡ ሰዎች ላይ እያስከተለ ያለውን አሉታዊ ተጽእኖ በግርድፍ ለመዳሰስ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ይህ መንገዶችን የመዝጋት ዘመቻ ከፖለቲካ፣ ማህበራዊ እና ህግ አንጻር ያለውን እንድምታ ምን ይመስላል፣ የሚለውን በአጭሩ ለማየት ነው፡፡ የጽሁፍ አቅራቢ ዋና ዓላማ እንደማንኛውም ሃላፊነት የሚሰማው ዜጋ የሚታዩ ጉድለቶችን እንዲስተካከሉ እንጂ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ዒላማ ለማድረግ ወይም የአያት ሪል እስቴትን መልካም ስምና ዝና ለማጉደፍ አይደለም፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአገራችንም ሆነ በከተማችን ደረጃ በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ እየተደረጉ ያሉት በርካታ እና ግዙፍ የመሰረት ልማቶች ግንባታ ዋና ዓላማ በኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ህይወት የተሳሰረ አንድ ጠንካራ የፖለቲካ ማህበረሰብ መፍጠር ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ ስሙ በተጠቀሰው እና በሌሎች አንድ አንድ የከተማዋ አካባቢዎች እየታዩ ያሉ እንቅስቃሴዎች የዚህ *"በኢኮኖሚ፣ በማህራዊ፣ እና ፖለቲካዊ የተሳሰረ ህብረተሰብ መፈጠር"* ዓላማ ተቃራኒ እና አፍራሽ ሲሆኑ ይታያል፡፡

ወደተነሳንበት ርዕሰ ጉዳይ በቀጥታ ልመለስና በአያት ሪል እስቴት ውስጥ እጅግ ሰፊ በሆነ መሬት ላይ ቢያንስ ከ6000 በላይ የሆኑ የተለያየ ዓይነት እና ስፋት ያላቸው ግዙፍ ቤቶች ይገኛሉ፣ በእነዚህም ቤቶች ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ቤተሰቦች ይኖራሉ ፡፡ አያት ሪል እስቴት በአገራችን የሪል እስቴት ልማት ውስጥ ፋና ወጊ የሆነውን ያህል አሁን አሁን ከመሬት አጠቃቀም እና የሊዝ ሃሳብ ጋር ተያይዞ አሉታዊ ተጽዕኖዎች ሲፈጠር ይታያል፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአያት መንደር ባሉ ሁሉም ዞኖች ማለት ይቻላል ለህዝብ ክፍት መሆን የሚገባቸው ስፋታቸው ከ12 ሜትር በላይ የሆኑ መንገዶች ሲኖሩ እነዚህ መንገዶች የነዋሪው ህዝብ ጥያቄ ነው በሚል ሽፋን በጥቂት ግለሰቦች አነሳሽነት ዘመቻ በሚባል መልኩ ከላይ እንደተገለጸው በትልልቅ የብረት በሮች እየታጠሩ ይገኛሉ:: አንዳንዶች መንገዶች በተለይም ከአዋሳኝ ነዋሪዎች ጋር የሚገናኙ በሮች ሙሉ በሙሉ የተዘጉ ሲሆን የተወሰኑት በሮች ደግሞ አያት ሪል እስቴት ውስጥ ላሉ ነዋሪዎች ብቻ እንዲያስተላልፍ በታዘዙ የጥበቃ ሰራተኞች ይከፈታሉ፡፡ ለዚህ የመተላለፊያ መንገዶችን የመዝጋት ዘመቻ ላይ ላዩ እየተሰጠ ያለው ምክንያት "የፀጥታ ጉዳይ " የሚል ሲሆን ከዚህም አለፍ ሲል "ይህ አካባቢ የሊዝ ይዞታ ስለሆነ ማንም ምንም ማለት አይችልም፣ እኛ በቦታው እንደፈቀድነው የመሆን መብት አለን" የሚል መሰረት የሌለው የህግ ክርክር ለማቅረብ ይሞክራል፡፡

ለማንኛውም የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ወደ እውነተኛው የመንገድ መዝጋት ዘመቻ ዋና ምክንያት እና ወደ ህጋዊ መከራከሪያ ነጥቦች ከመግባቱ በፊት አያት ሪል እስቴት ውስጥ ስላሉ ቤቶች አንዳንድ ጥሬ ሀቆች ማስቀመጡ ለያዝነው ንዑስ ጉዳይ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ሁሉም የአያት መንደር ቤቶች አሁን በአ.አ ከተማ ካለው የመሬት ቆዳ ስፋት አንጻር ሲታይ በቂ ስፋት ያላቸው ሲሆኑ ሁሉም ቤቶች የየራሳቸው የሆነ ግቢ እና አጥር ያላቸው፣ ከሪል እስቴት ጥበቃዎች በተጨማሪ ብዙዎቹ የግላቸው ጥበቃ ያላቸው እና አጥሮቻቸው በ "አደገኛ አጥር" የታጠሩ ናቸው፡፡

ታዲያ እነዚህ የሰፈር እና የግል ጥበቃ እንዲሁም በአደገኛ አጥር ታጥረው የሚኖሩ ሰዎች ለምን ይሆን ተጨማሪ ሰፋፊ የአካባቢ አጥሮች ፈጥረው በግቢ ላይ ሌላ ግቢ ጨምረው መኖር የፈለጉት? ይህን ለማወቅ ብዙ ማሰብ የሚያስፈልገው አይደለም ፤ እነሱ እንደሚሉትም በፀጥታ ምክንያት አይደለም፡፡ በዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እምነት የዚህ ጉዳይ ዋና ምክንያት የመንግስትና የህዝብ ንብረት የሆነውን መንገድ በመዝጋት የአካባቢውን ቤቶች የኪራይ እና የሽያጭ ዋጋ አርቴፊሻል በሆነ መልኩ ለማናር ሆን ተብሎ የተደረገ ስግብግብነት ነው፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል የሚል ተገቢ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፣ እንደሚታወቀው እነዚህን ቤቶች የሚገዙ ወይም ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች በፋይናንስ አቅማቸው ከፍ ያሉ ሲሆኑ እነዚህ ሰዎች ካላቸው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ህይወት አንጻር ሲታይ የበለጠ ሰፋፊ ቦታ እና የበለጠ ደህንነት እንዲሰማቸው የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ስለዚህም የአያት አከራዮች እና ሻጮች ከግል መኖሪያ ቤቶቻቸው በተጨማሪ

ለገበሮዎችም ሆነ ለተከራዮች በህገ ወጥ የዘጓቸውን መንገዶች ለተጨማሪ ገፀ በረከትነት ለማቅረብ እና ዋጋ ከፍ አድርጎ ለመደራደሪያነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡ ይህንን እውነታ በቀላሉ ለማረጋገጥ የሚቻለው እነዚህ ሰዎች በአሁኑ ሰዓት ዘግተው በያዟቸው መንገዶች የግል መጠቀሚያ ተሽከርካሪዎች ቆመው ይታያሉ፣ ልጆቻቸውም ብስክሌት ይለማመዳሉ/ይነዳሉ ፤ ለአካል እንቅስቃሴ መስሪያ ወዘተ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ የሚገርመው ነገር ሁሉም የአያት ቤቶች ማለት ይቻላል በራሳቸው ግቢ ውስጥ በትንሹ 2 እና ከዚያ በላይ መኪና ማቆም የሚችል በቂ ቦታ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

ይህ መንገዶችን በመዝጋት አርቴፊሻል በሆነ መልኩ የሽያጭ እና የኪራይ ዋጋ ለማናር የሚደረግ ጥረት የሌሎችን ሰዎች በተለይም በሪል እስቴቱ አጎራባች በሚኖሩ ዜጎች ላይ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ህይወት ቀውሶችን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ለማሳያነት ብንወስድ ዞን 3 ተብሎ ከሚጠራው የአያት ሪል እስቴት ድንበር ውጪ (በ30 ሜትር ርቀት) ላይ የሚኖሩ በርካታ ዜጎችን ሁኔታ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህ በዞን 3 አጎራባች በሆነው አካባቢ በርካታ ቤተሰቦች በህጋዊ መንገድ ከ 1996/97 ዓ.ም ጀምሮ በማህበር ተደራጅተው በሰሩአቸው ቤቶች ይኖራሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ቤተሰቦች ከሪል እስቴቱ ጋር ተያይዞ ሊገኝ ከሚችል የአካባቢ ልማት ትሩፋት ተጠቃሚ መሆን ሲገባቸው ከመተላለፊያ መንገዶች መዘጋት አንስቶ እስከ ሌሎች አይነት የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ሪል እስቴቱ እንቅፋት ሲሆን ይታያል፡፡

እነዚህ የሪል እስቴቱ አጎራባች የሆኑ ዜጎች በግላቸው ገንዘብ አውጥተው ከአያት ሪል እስቴት ጋር ካሉ መንገዶች ጋር የሚያገናኝ መንገድ ቢሰሩም የሰሩትን መንገድ ብዙ ሳይጠቀሙበት በዚህ መንገድ የመዝጋት ዘመቻ ሰበብ የመውጫ እና መግቢያ መንገዶቻቸው እየተዘጉ ለአላስፈላጊ መንገላታት ተዳርገዋል፡፡ ከዚህም አልፎ በሪል እስቴቱ እራሳቸውን አጥረው በሚኖሩት እና ከአጥሩ ውጭ በሚኖሩት አጎራባቾች በኢኮኖሚ አቅም የተለያዩ ነገር ግን የአንድ አገር ዜጎች መካከል አላስፈላጊ የመቃቃር እና የክፍፍል ስሜት እየፈጠረ ይገኛል፡፡

ይህም ድርጊት በአጥሩ ወስጥ እና ከአጥሩ ውጪ ያሉትን ታዳጊ ልጆች አብረው ተጫውተው አፈር ፈጭተው ውሃ ተራጭተው አንዱ አንዱን አውቆ የበለጠ ማህበራዊ ህይወት ትስስር እየፈጠሩ እንዳያድጉ እንቅፋት ሆኗል፡፡ እዚህ ላይ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው በፈረንሳይ አብዮት ጊዜ አንዲ ፈረንሳዊት ልዕልት የዳቦ ጥያቄ ላነሱ የዘመኑ

ሰልፈኞች “ለምን ኬክ አይሰጣቸውም?” እንዳለችው ሁሉ የአያት “የሃብታሞቹ” ልጆች ከአካባቢው ማህረሰብ ተገልለው አድገው በኋላ እንደ ፈረንሳዊቷ ልዕልት በአገራቸው በኢትዮጵያ ጉዳይ ባዕድ እንዳይሆኑ ያሰጋል ፡፡

ይህ በፀጥታ አሳብቦ መንገዶችን በመዝጋት በከተማዋ ደሴት መፍጠር በተወሰነ መልኩ ከእስራኤሎችና ፍልስጤሞች ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል፡፡ እንደሚታወቀው እስራኤሎች ከፀጥታ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ትልልቅ እና እረጃጅም ግንቦች ሰርተው ወደ ከተሞቻቸው ለሚገቡ እና ለሚወጡ የፍልስጤም ሰራተኞች መግቢያ በር አዘጋጅተው በፀጥታ ሀይሎቻቸው ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ የእኛዎቹም የአያት ነዋሪዎች አካባቢውን ሁሉ አጥረው የተወሰኑ መግቢያ እና መውጫ በሮች ላይ ብቻ የጥበቃ ሰራተኞችን አቁመው የአያት ነዋሪ ብቻ እንዲገባ እና እንዲወጣ ያደርጋሉ፡፡ የሚገርመው ነገር የእስራኤልና የፍልስጤሞቹን ሁኔታ ስናይ ሁለቱ ህዝቦች በብዙ መልኩ ልዩነት ያላቸው እና አብሮ ለመኖር የተቸገሩ ናቸው፡፡ የእኛዎቹ የአያት ነዋሪዎች ግን አጠገባቸው ካሉ ወገኖቻቸው በፀጥታ ሰበብ አጥር አጥረው ለብቻ መኖር መምረጣቸው በዚህም ሰበብ የአንድ አካባቢ ነዋሪዎች ለሁለት በመከፋፈል ልዩነት /ደሴት/ ለመፍጠር መሞከሩ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን የቆየውን አብሮ የመኖር ባህላችንን የሚጎዳ ተግባር መሆኑን መረዳት አያስቸግርም ፡፡

በነገራችን ላይ በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች የሚሰሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች (ኮንዶሚኒየም) ከዋናው የዜጎች የቤት እጥረት ችግር የማቃለል አላማ በተጨማሪ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሀብታም እና ደሃ ሰፈር ተብሎ የሚፈጠረውን ክፍፍልም ለማስቀረት የሚያግዝ ይመስለኛል፡፡ በዚህ ረገድ በእኔ እምነት በገርጂ አካባቢ ያሉት ሁለት አይነት ኮንዶሚኒየሞች (የመንግስትና የሰንሻይን) ጥሩ ምሳሌ ናቸው፡፡

ወደተነሳንበት የመተላለፊያ መንገዶችን የመዝጋት ጉዳይ ስንመለስ የአገራችን ህጎች እና የከተማችን መልካም ልማዳዊ አሰራሮች/ተሞክሮዎች እንዴት እየተጣሱ እንዳሉ እና ይህንን ጉዳይ በህግ እና በህግ ብቻ እንዴት መከላከል እና ማስቆም እንዳለብን እንመልከት፡፡

ሁሌም የህግ ጉዳይ ሲነሳ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ህገ መንግስት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 40(3) የንብረት መብት

በሚለው ድንጋጌ *"የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት"* የመንግስትና የህዝብ ብቻ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡ ስለዚህም በተፈጥሮ ሰዎችም ሆነ ህጋዊ ሰውነት ባላቸው ተቋሞች (ሪል እስቴቶችንም ጨምሮ) በእጃቸው ያለው መሬት ተጨማሪ ማብራሪያ እና ገለፃ ሳያስፈልገው መሬቱ የመንግስትና የህዝብ መሆኑን ያሳያል::

ይሁን እንጂ መሬትን ለማልማት እና ከመሬት የሚገኘውን ጥቅም ከፍ ለማድረግ ሲባል ይህ መሠረታዊ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ ሳይጣስ የተለያዩ ህጎች እና አሰራሮች ወጥተዋል፡፡ በዚህ ረገድ የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ እንደገና ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 272/1994 በተለይም አንቀፅ 2(7) *"የህዝብ ጥቅም"* በሚለው የማያሻማ ትርጉም *"በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ህዝቦች በመሬት ላይ ያላቸውን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የከተማ ልማትን በቀጣይነት ለማጎልበት አግባብ ያለው አካል በመሪ ፕላን ወይም በልማት እቅድ የህዝብ ጥቅም ብሎ የሚወሰነው ነው"* ይላል::

ከዚህ የህግ ድንጋጌ የሊዝ አስፈላጊነት የምንረዳው መንግስት እና ህዝብ ከመሬት አልሚዎች ይሁን ከሌሎች ወገኖች በሊዝ መልክ ከሚገኘው ሀብት (ገንዘብ) ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንጂ ህዝቡን በሊዝም ሆነ በሌላ አይነት አሰራር የመሬት ባለቤትነቱን ለማሳጣት አይደለም፡፡ ስለዚህም በአያትም ሆነ በሌሎች ሪል እስቴት የሚገኙ አልሚዎችም ሆኑ ነዋሪዎች ህዝብ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ይቅርና የመኖሪያ ቤቶቻቸው ያረፉበት ቦታም ጭምር የህዝብና የመንግስት መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም በየትኛውም የአገሪቱ አካባቢ የሚኖር ሰው በእጁ ያለውን መሬት ሲጠቀምበት ለበለጠ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ፋይዳ ላለው አገልግሎት የማዋል ሀላፊነት አለበት፡፡

ሌላው ህግ ደግሞ በተሻሻለው የአ.አ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 በጠቅላላ ድንጋጌ የነዋሪዎች መብት አስመልክቶ ሲያብራራ በተለይም አንቀፅ 7(2) *"ነዋሪዎች የከተማው አስተዳደር የሚሰጠውን አገልግሎት በእኩልነት፣ በግልፅነትና በፍትሀዊነት መርህ መሰረት የማግኘት መብት አላቸው"* ይላል:: ከዚህም አልፎ ይህ አዋጅ የከተማው አስተዳደር አላማዎች በሚዘረዝረው ክፍል ሁለት አንቀፅ 9(1)ላይ *"ብቁ ግልፅና ለነዋሪው ተጠያቂነት ያለበትን መልካም የአስተዳደር ሥርአት ቀልጣፋና ፍትሀዊ የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት እንዲሁም አስተማማኝ ፀጥታና ማህበራዊ ትስስር የተረጋገጠበት ከተማ የማድረግ"* ብሎ ይተነትናል:: ይሁን እንጂ ከፍ ሲል እንደተገለጸው ከነዚህ የህግ ድንጋጌዎች ተቃራኒ በሆነ መልኩ ለዚህ ፅሁፍ መነሻ በሆነው አካባቢ በ30 ሜትር ርቀት ላይ በሚኖሩ ሁለት

የአንድ ከተማ የህብረተሰብ ክፍሎች መንገድ እና ሌሎችም የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች እንዳያገኙ ከፍተኛ አድሎ እና ተፅእኖ እየተደረገ ይገኛል፡፡ (በነገራችን ላይ ከውሃ እና መብራት ጋር ተያይዞ በአያት ተጎራባች ነዋሪዎች ላይ የደረሰው እና እየደረሰ ያለው ተፅእኖ በሚቀጥለው ጊዜ ራሱን ችሎ በዝርዝር እመለስበታለሁ፡፡)

ከዚህ የመሬት እና የመንገድ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ ከኢህአዴግ የስልጣን ዘመን በፊት የወጡትን ህጎች ስናይ በመጀመሪያ የሚመጣው በአፄ ሀይለስላሴ ዘመነ መንግስት የወጣውና እስካሁንም ድረስ በአመዛኙ በስራ ላይ ያለው የፍታብሔር ህጉ ሲሆን በዚህ ህግ አንቀፅ 1446(ሀ) የህዝብ አገልግሎት ንብረቶች ተብለው ከተዘረዘሩ ውስጥ *"…. ጎዳናዎች እና መንገዶች….."* ይገኙባቸዋል፡፡ ከዚህም ወረድ ብሎ በተለይም በአንቀፅ 1457 (1) ማንኛውም ሰው ***"የአስተዳደር ክፍል ካልፈቀደ በቀር አንድ ሰው ለራስ ጥቅም ለህዝብ አገልግሎት ከተመደበው ንብረት አንዱን ክፍል በባለግልነት ለመያዝ አይችልም"*** ይላል:: እንግዲህ እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ይህ ህግ ሲወጣ መሬት የግል ንብረት በነበረበት ዘመን እንኳን ማንኛውም ሰው ባሻው ጊዜ ተነስቶ እንደመንገድ የመሳሰሉትን የህዝብ ንብረቶች አይዝም ማለት ነው፡፡ ጉዳዩን የበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው በአሁኑ ጊዜ መሬት የመንግስትና የህዝብ ነው ተብሎ ህገመንግስታዊ ድንጋጌ ጭምር ባለበት አገር እና ዘመን የተወሰኑ ሰዎች ህዝብ የሚተላለፍበትን መንገድ ዘግተው ለግላቸው ሲጠቀሙበት የመንግስት አካላት ዝምታ መምረጣቸውና በዚህም የተነሳ እነዚህ ህገወጥ ወገኖች የልብ ልብ ማግኘታቸው ነው፡፡

ይህ የፍትሀብሔር ህግ ከዚህ በተጨማሪ ማንም ሰው እነዚህን ድንጋጌዎች የጣሰ እና ለህዝብ አገልግሎት የተመደበን ንብረት ለራሱ ጥቅም ያዋለ እንደሆነ የአስተዳደሩ ክፍል ስላለው የመሻር መብት ሲያብራራ በአንቀጽ 1459 ላይ እንዲህ ይላል፡- ***"ተቃራኒ የሆነ ስምምነት ቢኖርም እንኳን ለህዝብ አገልግሎት የተመደበውን ንብረት አጠባበቅን የሚጎዳ ወይም የንብረቱን አገልግሎት ግብ የሚቃወመውን ማናቸውንም ስራ እንዲፈርስ ወይም ማናቸውም አሰራር እንዲቀር የአስተዳደሩ ክፍል በማናቸውም ጊዜ ለማዘዝ ይችላል"*** ይላል፡፡

እንግዲህ ህጉ ምን እንደሚል ከላይ ያየነው ቢሆንም በአያት ሪል እስቴት ውስጥ እየተደረጉ ያሉ የመንገድ መዝጋት ዘመቻዎች ግን እንኳንስ አስቀድመው የሌሎች ዜጎችን ጥቅም ሊያስቡ ይቅርና በተለያየ ጊዜ ድርጊቱ ህጋዊ እንዳልሆነ ከአካባቢው የአጎራባች ነዋሪዎች ቢነገራቸውም ካላዋቂነታቸው ወይም ማንአለብኝነታቸው ብዛት የተነሳ

ድርጊታቸው ህጋዊ እንደሆነ እና ይህ በሪል እስቴቶች አሰራር የተለመደ እንደሆነ በኩራት ይናገራሉ፡፡

የዚህ ፀሁፍ አቅራቢ ለእነዚህ ህገወጥ የመንገድ መዝጋት ዘመቻዎች ከመንግስት ፍቃድ እንደማይሰጥ ቢገምትም ምናልባት በቃል ወይም በዝምታ በመታለፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ዘንድ ስምምነት አግኝተው ከሆነ ይህ ስምምነት የጠቅላላ ህዝቡን ጥቅም በተለይም የአጎራባች ነዋሪዎችን ጥቅም የሚጎዳ ስለሆነ የሚመለከተው ወገን አይቶ አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ቢወስድ መልካም ይመስለኛል፡፡ በነገራችን ላይ በቅርቡ የአ.አ መስተዳደር ህገወጥ ግንባታዎችን እና ህገወጥ ንግድን የሚከላከል ራሱን የቻለ ተቋም ማደራጀቱ ይነገራል፡፡ ስለዚህም ይህ ተቋም ይህን በአያት ሪል እስቴት ውስጥ እየተደረገ ያለውን ህገወጥ መንገድ መዝጋት በማስቆም ረገድ ግንባር ቀደም ሚና መጫወት አለበት፡፡

ለማጠቃለል ያህል ማንኛውም ሰው የአገሪቱን ህግና የከተማውን ማስተር ፕላን በመፃረር የህዝብና የመንግስት ሃብት (መገልገያን) በማንኛውም መነሻ ምክንያት ለግሉ በመቆጣጠር የሌሎች ወገኖች መብት ለመጋፋት ህጋዊ መሰረት ይሁን ስልጣን እንደሌለው ሁሉ የዚህ ጽሁፍ መነሻና የችግሩ ባለቤት የሆኑት የአያት መንደር ነዋሪዎችም ከዚህ ውጭ እንዳልሆኑ ተገንዝበው ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ እና የተዘጉ መንገዶችን እንዲከፍቱ፣ ወደፊትም ከተመሳሳይ ድርጊት እንዲቆጠቡ እየጠየቅሁ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ህግ አስፈጻሚ አካላትም ለህዝብ መብትና ጥቅም ሲባል ህጋዊ ሃላፊነታቸውን በመወጣት የህዝብ ወገንተኝነታቸውን እንዲያሳዩ እንጠይቃለን፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ነገሮች በዚህ ከቀጠሉ ግን ነገም ሌሎቹ ዋና አውራጎዳናዎች በተመሳሳይ መልኩ እና ምክንያት እንደማይዘጉ ዋስትና አለ ብዬ አልገምትም፡፡

በመጨረሻም ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በአያት ዞን 3 አጎራባች በሆኑ ዜጎች ላይ የውሃና የመብራት በመሳሰሉ መሰረተ ልማቶች የደረሰውን እና እየደረሰ ያለውን ተጽዕኖ እና መጉላላት አስመልክቶ በዝርዝር እንደማቀርብ ቃል እገባለሁ፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ፣መረጃ፣ ሀሳብ ወይም መልስ መስጠት ለምትፈልጉ ወገኖች በጽሁፉ መጀመሪያ ላይ በተጠቀሰው ኢሜል አድራሻዬ ልታገኙኝ ትችላላችሁ፡፡